



ብሔራዊ የሴቶች ማብቃት እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ፖሊሲ

ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

ግንቦት 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

1.መግቢያ 3

2. የፖሊሲው መነሻዎች 5

3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ርዕይ፣ አላማዎችና መርሆዎች 8

4.የፖለሲ ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች 11

5. የፖሊሲ ቁልፍ የውጤት መስኮች 21

6. የፖሊሲ ማውጣት ስልጣንና የፖሊሲውን ተፈጻሚነት ወሰን 25

7. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች 25

8.ተዛማጅ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንብ እና ስምምነቶች 31

9.የቃላት ፍቺ 33

1.መግቢያ

ኢትዮጵያ የሴቶችን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ሴቶችን ለማብቃትና የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን መጠነ ሰፊ የህግ እና የፖሊሲ ማሻሻያዎች አድርጋለች። መንግስት የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በህገ መንግስቱ የሴቶች መብቶችን ለማስከበር ልዩ ድንጋጌዎችን በማካተት፣ ብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ በማውጣትና በመተግበር፣ የሴቶች የልማትና የለውጥ ፓኬጅና ስትራቴጅ በመንደፍ፣ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት እንዲሁም የአስር አመት የልማት እቅድ በማውጣት ሲተገብር ቆይቷል። ከዚህም በተጨማሪ ሴቶችን ማብቃትና ስርዓተ-ጾታን የተመለከቱ አለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች በመፈረምና በማጽደቅ የሀገሪቱ የህግ አካል በማድረግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ ፆታ እኩልነት ጉዳይ የአንድ ሀገር ፍትሃዊነት፣ ዘላቂ ልማትና ማህበራዊ እድገት መሰረታዊ አካል ነው። ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በአመራር ዘርፎች ሙሉ ተሳትፎ ሲያደርጉ ሀገራዊ እድገት የተፋጠነና የተመጣጠነ ይሆናል። በዚህ ረገድ የ“መደመር” እሳቤ ሁሉንም ማህበረሰብ ክፍሎች በማካተት፣ በመተባበርና በእኩል ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ አቀራረብ በመሆኑ የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

የመደመር እሳቤ ሴቶችን እንደ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን እንደ አጋርና እንደ ለውጥ አምጪ ኃይል በመመልከት በተለይ በሀገራችን በተካሄደው ሪፎርም በሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ላይ በተወሰደው እርምጃ እንደ ሀገር ታይቶ በማይታወቅ ድረጃ በሀገራችን አዲስ ምዕራፍ እንዲከፈት እና በማህበረሰብ ውስጥ የነበረው ለሴቶች አመራርነት የነበረው አሉታዊ አመለካከት በመሰረታዊነት እንዲቀየር አድርጓል፣

በኢኮኖሚ ተሳትፎ ሴቶች ጎታች ከነበረው አስተሳሰብ ተላቀው የሀብት ባለቤት እንዲሆኑ ተደርጓል፣ በትምህርትና በማህበራዊ ተግባራት ውስጥ እኩል እድል እንዲያገኙ አድርጓል። በዚህም የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ ፆታ ቁልፍ እርምጃዎች የመደመርን እሴቶች መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ፣ አካታችና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በተግባር እንዲተገበሩ ተደርጓል። ስለሆነም የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ ፆታ ፖሊሲዎች የመደመርን እሴቶች መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ፣ አካታችና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በሁሉም ደረጃና ዘርፍ በስፋት ሊተገበሩ ይገባል።

የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት በራሱ የእድገትና የልማት ዓላማ ከመሆኑም በላይ በሴቶችና ወንዶች መካከል እኩል መብት፣ ኃላፊነት እና እድሎችን የመፍጠር፣ የሰብዓዊ መብትና ማህበራዊ ፍትህን የማስፈን ጉዳይም ነው። ዜጎች ጾታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የመጠበቅ መብት ያላቸው ቢሆንም ስር በሰደዱ አሉታዊ አመለካከቶች፣ ማህበራዊ ወጎች፣ በሴቶችና በወንዶች መካከል ባለው የተዛባ የስርዓተ-ጾታ ግንኙነት እና ወዘተ ምክንያቶች ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ይፈፀማሉ። በዚህም ምክንያት ዜጎች ለበርካታ አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች ይጋለጣሉ።

ብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ ሲሆን በ2011 ዓ.ም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የፖሊሲው አፈጻጸም፣ ውጤቶችና ተግዳሮቶችን የተመለከተ ሀገራዊ ጥናት ማድረግ ችሏል። የጥናቱ ውጤትና ምክረ-ሃሳቦች ነባሩን ፖሊሲ መከለስ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመላክቱ ሆነው በመገኘታቸው ነባሩ ብሔራዊ የሴቶች ፖሊሲ ሊመልሳቸው ያልችሉ ጉዳዮች እንዲሁም አሁን ሃገራችን የደረሰችበት የእድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ እና የህብረተሰቡን ጥያቄ ሊመልስ በሚችል መልኩ የቀድሞውን ፖሊሲ መከለስ አስፈላጊ ሆኗል።

ከዚህ በተጨማሪ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን የተመለከተ ወጥና ጥቅል ትርጉም የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታና እሴቶች በተከተለ መልኩ የሚተረጉም የፖሊሲ ማዕቀፍ ባለመኖሩና አዳዲስ መልክ ያላቸው እንደ በይነ መረብና በቴክኖሎጂ የታገዙ ጥቃቶች እየጨመሩ በመምጣታቸው ማንኛውም ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተቀባይነት እንደሌለው ለማረጋገጥ፤ ሰብአዊ መብቶችን ለማክበርና ለመጠበቅ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የፖሊሲ አቅጣጫ እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል፤

ይህ ብሔራዊ የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ-ጾታ እኩልነት ፖሊሲ የሴቶችን ሁሉንተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የሴቶችን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ሴቶች በሁሉም የልማት መስኮች በመሪነትና ውሳኔ ሰጪነት ሚና ለማሳደግ፣ ጥቃትን የማይታገስ ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ተጋላጭ የሆኑ ወገኖች ፈጣንና ፍትሐዊ ምላሽ የሚሰጥ ተቋማዊ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል አቅጣጫዎችንና ውጤቶችን የያዘ ፖሊሲ ነው፤

በመሆኑም ሴቶች በሀገር ኢኮኖሚና ዴሞክራሲ ግንባታ እና በማህበራዊ ልማት ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ መዳረሻውን በሁሉም ዘርፍ የስርዓተ-ጾታ እኩልነት የተረጋገጠባት እና ጥቃትን የማይታገስ ማህበረሰብ ለመገንባት ይህ የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ-ጾታ እኩልነት ፖሊሲ ተግባራዊ ይደረጋል።

2. የፖሊሲው መነሻዎች

በ1986 ዓ.ም የወጣው ብሄራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ በወቅቱ የነበረውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት በነበረ የትግበራ ሂደት የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ተችሏል። በኢኮኖሚው መስክ የሴቶች የመሬት ተጠቃሚነታቸውን በማሳደግ፣ የሴቶችን ሥራ አጥነት በመቀነስ፣ የሴቶችን የፋይናንስ ተሳትፎ በማሳደግ፣ በህብረት ስራ ተሳትፏቸውን በማስፋት፣ የንግድ እድገታቸውን እና የስራ ፈጠራ ክህሎታቸውን በማሻሻል እና የስራ እድልን በማሳደግ ረገድ ጉልህ እድገቶች ታይተዋል። በማህበራዊ መስክ በትምህርት የሴቷን ተሳትፎ በሁለንተናዊ መልኩ እንዲጠናከር፣ የሴቶች ተደራራቢ የጤና ችግሮችን በመፍታት የእናቶችና የህጻናት ሞት በመቀነስ፣ በየአካባቢው ያሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች እንዲቀንሱ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች አስፈላጊውን አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ በአጠቃላይ ሴቶች ያሉባቸው ማነቆዎች እንዲፈቱ በማድረግ አበረታች ስኬቶች ተመዝግበዋል። በተጨማሪም የሴቶች የውሳኔ ሰጭነትና ተሳትፎ በፌዴራል ህግ አውጪ፣ በህግ አስፈጻሚውና በህግ ተርጓሚው ተሳትፏቸው እንዲያድግ ማድረግ ተችሏል። ይሁን እንጂ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስኮች የሴቶች እኩል ተሳታፊነት፣ ተጠቃሚነት እና የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አንጻር አሁንም ተግዳሮቶችና ውስንነቶች ይስተዋላሉ።

የሴቶች ማብቃትና የስርዓተ ፆታ እኩልነት ፖሊሲ ከመደመር እሳቤ አኳያ በጥልቀት በማየት እና ባለፉት የለውጥ አመታት በመደመር መንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት በተወሰዱ እርምጃዎች የስርዓተ ፆታን እኩልነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ አምርታዎች የታዩ ሲሆን እነዚህን ውጤቶች ይበልጥ መሰረት ለማስያዝ፤ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች የሴቶችን ተሳተፎ፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና አክኡልነት ፍትሃዊና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ያለው ፍላጎት በሚገባ ተረድቶ በየደረጃው ተግባራዊ እንዲያደረግ እና ለረጅም ጊዜያት ሴቶች በባህላዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ስርዓቶች ውስጥ ሲያጋጥማቸው የቆዩትን መድልዎዎችና እገዳዎች ምክንያት በትምህርት፣ በአመራር፣ በኢኮኖሚ ተሳትፎና በውሳኔ ሰጪነት ላይ

ያላቸውን ተሳትፎ ዝቅ ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ በማሻሻል ሴቶች በሁሉም ዘርፍ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ የፖሊሲው መሰረታዊ መነሻ ይሆናል። ሌላው መነሻ ምክንያት መደመር የሚያበረታታው አካታችነትና መተባበር በመሆኑ አንዱ ሌላውን ሳያገል ሁሉንም በጋራ ማሳተፍና ለጋራ ግብ አብሮ መስራት ስለሚያስፈልግ ሴቶች የሴቶችን ጉዳይ በተናጠል ለብቻቸው የሚያሳኩት ባለመሆኑ የወንዶች አጋርነትም ያስፈልጋል፤ ስለሆነም አካታችነትና ትብብር አሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል።በማህበራዊ ዘርፍ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና እኩልነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጉዞ የሚገቱት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ስር ከሰደዱ ማህበረሰዊና ባህላዊ፣ መዋቅራዊ እና ተቋማዊ መንስኤዎች የሚቀዱ ናቸው። በአንድ በኩል የማህበረሰብ ወግ ምክንያት ሴቶች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምትና በራስ የመተማመን ብቃታቸው በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ የሴት ተማሪዎች የሁለተኛና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ እና በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በኢንጂነሪንግና በሂሳብ ትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን እደርጎቷል፣ በሌላ በኩል፣ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተቀረጹ የህግና የተቋም ስርዓቶች የራሳቸው መዋቅራዊ ክፍተት አለባቸው። ጾታ-ተኮር ጥቃቶችን በአንድ ወጥና ጥቅል መልኩ የሚተረጉም የህግ ማዕቀፍ አለመኖር፣ የህግ አስፈጻሚ አካላት የአፈጻጸም ክፍተት እና ለተጎጂዎች የሚሰጡ ሁለንተናዊ የህክምና፣ የስነ-ልቦና እና የህግ ድጋፎች በጥራትና በተደራሽነት አለመቀናጀት ፈጣንና ተመጣጣኝ ፍትህ እንዳይሰፍን ዕንቅፋት ሆነዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ የሴት አደረጃጀቶች እና የልማት ህብረቶች ነጻ፣ ገለልተኛና ጠንካራ ተቋማዊ አቅም ኖሯቸው የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም ማስከበር እንዲችሉ የሚደረገው ስልታዊ ድጋፍ ማነስ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት እነዚህን አደረጃጀቶች እንደ ዋና የልማት አጋር አድርገው አለማሳተፋቸው ችግሮቹን ይበልጥ ስር እንዲሰዱ አድርጓቸዋል።

በኢኮኖሚ መስክ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ተስማሚ አሰራሮች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች መኖራቸው፣ ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ በግል ተቋማትና በኢንዱስትሪዎች ወጥነት ባለው መንገድ ተፈጻሚ አለመደረግ፣ አካታች የሆነ የፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊነት የተጠናከረ አለመሆን፣ በኢ-መደበኛ የንግድ መስኮች ላይ የተሰማሩ ሴቶችን ወደ መደበኛው የንግድ ስርዓት እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመተግበር፣ ክፍያ የማይፈፀምባቸውና ዕውቅና የማይሰጣቸው የእንክብካቤ እና የቤት ውስጥ ስራዎችን በኢኮኖሚው ውስጥ የሚካተትበት ስርዓት አለመዘርጋት፣ ከስደት ተመላሽ ሴቶችን የማቋቋምና የማጠናከር ስራዎች አጥጋቢ አለመሆን ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው።

በአመራርና ውሳኔ ሰጪነት የተመዘገቡ ጉልህ አገራዊ ውጤቶች ቢኖሩም በየደረጃው የሴቶች ተሳትፎ አለማደግ፣ ሴቶች በሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት፣ በምርጫ፣ በበጎ ፍቃድ አገልግሎትና በሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች ላይ ያላቸው ሚና አጥጋቢ አለመሆን፣ እንዲሁም በሴክተሮች የሥርዓተ-ፆታ ተቋማዊነት እና የተጠያቂነት አሰራር አለመጠናከር፣ የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎች፣ የሕግ ማዕቀፎች ክፍተትና አፈጻጸም ውስንነቶች መኖሩ፣ በገጠር እና በአርብቶ-አደር ሴቶች ላይ የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ተግዳሮቶችን በበቂ ሁኔታ ምላሽ የሚሰጡ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና የህግ ማእቀፎች አለመኖራቸው፣ የባለድርሻ አካላት ትብብርና ቅንጅት አለመጠናከር፣ ከፖሊሲና ከህግ ማዕቀፎች አንጻር የተስተዋሉ ክፍተቶች ናቸው።

ለእነዚህ ክፍተቶች ዋና መንስኤዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የሚስተዋሉ ስር የሰደዱ የተዛቡ አመለካከቶች፣ የፖሊሲ፣ የህግና የአሰራር ማዕቀፎች ክፍተት፣ ለሴቶች ምቹ ከባባዊ ሁኔታ አለመፍጠር፣ እንዲሁም ይህንን ችግር ለመፍታትና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በቂ መዋቅራዊ አደረጃጀት አለመኖርና አለመጠናከር ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች ለመፍታት የሴቶችን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅና እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ ይደረጋል።

3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ ርዕይ፣ አላማዎችና መርሆዎች

3.1 የፖሊሲው አስፈላገኒት

የብሔራዊ ሴቶች ፖሊሲን ለማሻሻልና ብሄራዊ የሴቶች ማብቃት እና የስርዓተ-ጾታ እኩልነት ፖሊሲ ያስፈለገበት መሰረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- እንደ ሀገር የትኩረት አቅጣጫ ዎቻችን የቤተሰብ ብልጽግና ማረጋጋጥ ስለሆነ ሴቶችን ማዕከል ተደርገው የሚሰሩ ስራዎች ስርዓተ ጾታ እኩልነት የሚያረጋግጥ ስራዎች መስራት በማስፈለጉ፣
- የቀድሞው ብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ የስርዓተ-ጾታን ጉዳይ የሴቶች ጉዳይ ብቻ አድርጎ መውሰድና የወንዶችን ተሳትፎ ጉልህ ሚና በግልጽ ባለማመላከቱ፣
- ኢትዮጵያ ከብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ መውጣት በኋላ ከተቀበለቻቸው አዳዲስ ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረጉ አለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ በማስፈለጉ፣
- በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስኮች ላይ የሴቶች እኩል ተሳታፊነት ተጠቃሚነት እና የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አንጻር ሰፊ ክፍተቶች በመኖራቸው፣
- ስርዓተ-ጾታ እኩልነት የሚመለከቱ ሕገ-መንግስቱን ጨምሮ ሌሎች ህጎች ከፖሊሲው በኋላ መውጣታቸው፣እና ተቋማት በመደመር እሳቤት በተከተለ መንገድ ፖሊሲዎቻቸውን ማሻሻያ በማድረጋቸው፣
- ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን በአግባቡ ለመከላከል፣ ጥበቃና ምላሽ ለመስጠት ዘርፈ ብዙና የተቀናጀ ስራ እንዲሁም በዕውቀትና በመረጃ ላይ የተመሰረተ የባለድርሻ አካላትን የማስተባበር ስራና የትብብር ማዕቀፍ በማስፈለጉ፣
- ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን የተመለከተ ወጥና ጥቅል ትርጉም የሚሰጥ የፖሊሲ ወይም የህግ ማእቀፍ እንዲኖር በማስፈለጉ፣
- በሴክተሮችና በየደረጃው ባለው መንግስታዊና የግሉ ዘርፍ የስርዓተ-ፆታ ተቋማዊነት እና የተጠያቂነት የአሰራር ስርዓት በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ ባለመደረጉ፣

- የሴት አደረጃጀቶች ተቋማዊ ብቃት የተጠናከረ አለመሆንና የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ቁመና ላይ ባለመሆኑ፣
- ልዩ ትኩረት ለሚሹ ሴት አካል ጉዳተኞች እና ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች ምላሽ መስጠት በማስፈለጉ፣
- ከዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ሀገራዊ እቅድ ጋር ለማስተሳሰር ሴቶች በዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ በመረጃ ተደራሽነት፣ በዲጂታል ክህሎትና በኢኮኖሚ ተሳትፎ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እና ሴቶች በትምህርት፣ በስራ፣ በንግድና በአመራር ዘርፎች የበለጠ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማድረግ ዲጂታል 2030 የሚፈልገውን አካታችና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ፣
- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በሴቶች ላይ እያስከተሉ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ መሰረት በማድረግ ቀጣይ እርምጃዎችን መውሰድ በማስፈለጉ፣
- የአየር ንብረት ለውጥ፣ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች በስርዓተ-ጾታ እኩልነት ላይ እያስከተሉ ያለውን ተጽዕኖ መሰረት በማድረግ ቀጣይ እርምጃዎችን መውሰድ በማስፈለጉ ይህ ፖሊሲ እንዲወጣ ተደርጓል።

3.2 የፖሊሲው ርዕይ

በሁሉም ዘርፍ የስርዓተ-ጾታ እኩልነት የተረጋገጠባት እና ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የማይፈጸምባት ኢትዮጵያን ማየት።

3.3 የፖሊሲው መርሆዎች

- አጋርነት፡- የፖሊሲው አፈፃፀም በመንግስት፣ በህብረተሰቡና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ዘርፈ ብዙ ትብብር፣ ቅንጅትና አሰራር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ግልጸኝነት፡- የሚተገበሩት ስራዎች ግልጽ በሆነ የአሰራር ስርዓት ይመራሉ፣
- ተጠያቂነት፡- የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን ከማስተግበር አንጻር ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይደረጋል፣

- እኩልነትና ፍትሃዊነት፡- ፖሊሲው በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በዘርና በአካል ጉዳተኝነት ልዩነት ሳይደረግ በእኩልነትና በፍትሃዊነት ይተገበራል፣
- አሳታፊነት፡- የህብረተሰቡና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ባለቤትነት እንዲጎላ ይደረጋል፡፡
- ጥቃትን አለመታገስ፡- ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ሁኔታ ተቀባይነት እንዳይኖረው ይደረጋ፣
- ምላሽ ሰጪነት፡- ለስርዓተ ፆታ እኩልነት፣ ለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተገቢው ምላሽ እንዲሰጥ ይደረጋል፣
- ተጎጂን ማዕከል ማድረግ፡- ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች የተጎጂዎችን ፍላጎት ያማከለ ሆኖ በተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው ላይም ተጨማሪ ስጋትም ሆነ ጉዳት እንዳያደርሱ ይደረጋል፣
- አካታችነት፡- የሚሰጡ ሁሉም አገልግሎቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ምላሽ የሚሰጥና ተጨማሪ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተጋላጭ የህብረተስብ ክፍሎች ምቹ እንዲሆኑ ይደረጋል።

3.4 የፖሊሲው ዋና ዓላማ

በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉትን ስር የሰደዱና የተዛቡ አመለካከቶች በመቅረፍ፣ ለሴቶች ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ መዋቅራዊ አደረጃጀቶችንና ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጠናከርና ጥቃትን የሚጠየፍ ማህበረሰብ በመፍጠር በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ መስኮች የሴቶችንና የወንዶችን እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ።

ዝርዝር ዓላማዎች

- በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ የሴቶችንና የወንዶችን እኩል ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣
- የሴቶችን የመሪነትና የውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎና ሚናቸውን ማሳደግ፣

- የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈን አዎንታዊ የሆኑ ባህላዊ እሴቶች እንዲስፋፉና ፆታን መሠረት ላደረገ ጥቃት አስተዋፅዖ በሚያደርጉ አሉታዊ ማህበራዊ ወጎች፣ አመለካከቶችና ሚናዎች ላይ ስር ነቀል ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ፣
- የስርዓተ-ጾታ ተቋማዊነትና የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት፣
- ጾታን መሰረት ካደረገ ጥቃትና ሌሎች የመብት ጥሰቶች ጋር በተገናኘ የሚሰጡ አገልግሎቶች ምላሽ ሰጪ፣ ተደራሽ እና ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ።

4.የፖለሲ ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች

4.1. የሴቶች መብትና ደህንነት ማስጠበቅ

ኢትዮጵያ የሴቶችን መብት ለማስከበርና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ በህገ-መንግስቱ የተደነገጉትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መሠረት በማድረግ ፈርማ የተቀበለቻቸውና ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍና አህገረ አቀፍ ስምምነቶች በሚፈለገው ደረጃ ተፈፃሚ ባለመሆናቸው፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ክፍተት፣ የተዛቡ አመለካከቶችና የግንዛቤ እጥረት፣ የህግና የፖሊሲ ክፍተቶች፣ በሴቶች መብት ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት አለመጠናከር፣ የሚመለከታቸው አካላት ድርሻቸውንና ሚናቸውን በሚገባ አለመወጣት እና የመረጃና የጥናት ስራዎች በተገቢው መንገድ አለመደራጀት የሴቶችን መብትና ደህንነት ለማስከበር አዳጋች ሆኗል። በመሆኑም የሴቶችን መብትና ደህንነት በማስከበር ረገድ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- በህገ መንግስቱ የተደነገጉትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መሠረት በማድረግ በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ ፈርማና አፅድቃ የተቀበለቻቸው ስምምነቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
- በሴቶች መብት ጥሰት ዙሪያ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶችና የግንዛቤ እጥረት ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣
- የሴቶችን መብትና ደህንነትን የሚጥሱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና መጤ ባህሎችን ለመከላከልና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

- ለሴቶች የመብት ጥሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች በጥናት እንዲለዩና የህግ ማሻሻያዎች እንዲደረጉና እንዲተገበሩ ይደረጋል፣
- የሴቶች መብትና ደህንነት ለማስከበር ሴቶች በሰላምና ደህንነት ማስከበር ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- በሴቶችና ታዳጊዎች ላይ የሚፈፀም የመብት ጥሰት ለመከላከል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመረጃ ማደራጀትና መተንተን ስርዓት በመዘርጋት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፣
- በሰብዓዊ መብት ላይ የሚሰሩ ተቋማትና አደረጃጀቶች እንዲጠናከሩና ድጋፍ እንዲደረግላቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- የሴቶች የሙያና የጾታ አደረጃጀቶች እንዲጠናከር በማድረግ እና ባልተደራጁባቸው አካባቢዎች በማደራጀት መብትና ደህነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣

4.2 ሴቶችን በኢኮኖሚ ማብቃት

ሴቶች በዋነኝነት መደበኛ ባልሆኑ ሥራዎች ላይ መሰማራታቸው፣ በመደበኛው ክፍለ ኢኮኖሚ ያላቸው ድርሻና ተጠቃሚነት አነስተኛ መሆን፣ ክፍያ የማይፈፀምባቸውና ዕውቅና የማይሰጣቸው የእንክብካቤ እና የቤት ውስጥ ስራዎች ጫና መኖርና እውቅና የተሰጣቸው አለመሆኑ፣ በግብርና፣ በቴክኖሎጂ፣ በኢንዱስትሪ፣ በገቢና ወጭ ንግድ፣ በስራ ፈጠራ እና ቅጥር ላይ ጉልህ የሆኑ የስርዓተ-ፆታ ክፍተቶች ይታያሉ። በመሆኑም እነዚህንና ሌሎች ችግሮችን በመቅረፍ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ኢኮኖሚያዊ እድሎችን የሚያስፋፉ አንዲሁም የስራ ፈጠራ አስተሳሰብና ክህሎትን የሚያበለፅጉ ስርዓቶች ይዘረጋሉ፣
- የሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነትና የንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአሰራርና የህግ ማዕቀፎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
- ለስርዓተ-ጾታ እና ሴቶች ጉዳይ ምላሽ የሚሰጥ የብድርና የቁጠባ አገልግሎትና አካታች የፋይናንስ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፣

- በሴቶች የሚመሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች በሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የፋይናንስ ስርዓት፣ ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ የንግድ ልማት አገልግሎቶች እና የገበያ ትስስር ድጋፍ ይደረግላቸዋል፣
- የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓቱ ሴት አርሶ-አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ እንዲተገበርና ሴቶች በግብርናው መስክ እንዲሳተፉና እንዲጠቀሙ ይደረጋል፣
- ሴቶችን ከኢ-መደበኛ ወደ መደበኛ የኢኮኖሚ መስክ እንዲሸጋገሩ የሚያስችሉ የፖሊሲ፣ የህግና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፣
- ሴቶችን በገቢና ውጭ ንግድ፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በአገልግሎትና በግብርና ዘርፍ በሰፊው ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ሴቶችን በቴክኖሎጂ ዘርፍ አቅማቸውን የማጎልበት፣ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ለሴቶች ተስማሚ፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ የሚሆኑበት ስርዓት ይዘረጋል፣
- የቤት ውስጥ እና ክፍያ የማይፈጸምባቸው የእንክብካቤ ሥራዎች ዕውቅና እንዲሰጣቸው፣ የሥራ ክፍፍል እንዲደረግ፣ የሥራ ጫና እንዲቀነስና የማካካሻ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፣
- ልዩ ትኩረት የሚሹ ሴት አካል ጉዳተኞችን እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን በተለየ መልኩ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

4.3 ማህበራዊና መሰረተ- ልማት አገልግሎቶች

4.3.1 ትምህርት አገልግሎት

የትምህርት ዘርፉ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነትን በመቀነስ ረገድ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ለውጥ ያስመዘገበ ቢሆንም በአንደኛ ደረጃ የመጠነ-ማቋረጥ፣ በሦስተኛና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥርዓተ-ፆታ ክፍተቶች መኖር በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ሴቶች እና ልጃገረዶች በተማሪነት፣ በመምህርነትና በአካዳሚክ ሃላፊነት ተሳትፏቸው አናሳ መሆን፣ ለሴቶች ምቹ የሆነ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣

ኢንጂነሪንግና ሂሳብ ዘርፍ ተሳትፏቸውን የሚያበረታታ ስርዓት አተገባበር ውስንነት መኖር ከትምህርትና ስልጠና ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ችግሮች ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈንና አካታች ሥርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ የመማር ማስተማር ሥርዓት ስርዓት እንዲዘረጋና ምቹ የትምህርት አካባቢ እንዲኖር ይደረጋል፣
- በሁለተኛና በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የሴቶችን ተሳትፎ እና ውጤታማነት ማሳደግ የሚያስችሉ አዎንታዊ የድጋፍ እርምጃዎች ይተገበራሉ፣
- የመጀመሪያ፣ መካከለኛ፣ ሁለተኛና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርትና ስልጠና ለሴቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- ለሴት ተማሪዎች ተስማሚ የሆኑ የንፅህና መጠበቂያ በአገልግሎት ተቋማት በሁሉም ትምህርት ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲስፋፋ ይደረጋል፣
- በሳይንስ፣ ቴክኖሎጅ፣ ኢንጂነሪንግና ሂሳብ ዘርፍ የሴቶችን ተሳትፎ ሊያሳድግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣
- የተቀናጀ የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምርት ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል።

4.3.2 የጤና አገልግሎት

ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት የእናቶችንና የህጻናትን ሞት ለመቀነስ፣ የክትባትና የቅድመ-ወሊድ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት እንዲሁም የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በመተግበር በሴቶች ጤና ላይ ተጨባጭና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደነቅ ስኬት አስመዝግባለች። ይሁን እንጂ ይህ የተገኘው የጤና ስኬት ዘላቂና ፍትሃዊ እንዳይሆን የሚያደርጉ መዋቅራዊ ክፍተቶች አሁንም በስፋት ይስተዋላሉ። የጤና አገልግሎቶች ለሴቶች በተሟላ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸው፣ ተደራሽ በሆነባቸው አካባቢዎችም የሠለጠነ የሰው ኃይል፣ የመድሃኒትና ቁሳቁሶች፣ የንፅህና መጠበቂያ እንዲሁም ሌሎች ግብዓቶች ዕጥረት መኖር፣ ሴቶችን በተለየ የሚያጠቁ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ግንዛቤ፣ የመከላከል ሥርዓትና የህክምና አገልግሎት ውስንነት መኖር፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል እናቶች በጤና ተቋማት አለመውለድ፣ የቅድመና የድህረ ወሊድ ክትትል ዝቅተኛ መሆን፣ ለሴቶች በተለይ ለታዳጊ ወጣት ሴቶች የሚሰጡ የስነ-ተዋልዶ ጤናና

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች ተደራሽነት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ በትምህርት ቤቶችና በስራ ቦታዎች ለሴቶችና ታዳጊ ሴቶች የንፅህና መጠበቂያ አቅርቦትና ምቹ ቦታዎች በተሟላ መልኩ አለመኖር በጤናው ዘርፍ የተስተዋሉ አንኳር ችግሮች ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ሁሉም የጤና አገልግሎቶች ሥርዓተ ጾታን ያገናዘቡ፣ አካታችና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- የእናቶችና ህጻናትን ሞት ለመቀነስ እናቶች በጤና ተቋማት እንዲወልዱና ጥራት ያለው የቅድመ እና ድህረ ወሊድ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- ተስማሚ የሆኑ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተደራሽነትና የስነ-ተዋልዶ ጤናና ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላልና የመቆጣጠር አገልግሎት እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- በሴቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግር እያደረሱ ያሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን (የማህፀን መውጣት፣ ፊስቱላ፣ የማህፀን ጫፍና የጡት ካንሰር) የተለየ ትኩረት በመስጠት ችግሩን ለመከላከልና ተገቢውን የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ሴቶች ጤናማ እና የተስተካከለ አካላዊና አዕምሯዊ ዕድገት እንዲኖራቸው ለማስቻል ሥርዓተ ጾታን ያገናዘበ የሥነ ምግብ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- ለሴቶችና ታዳጊ ሴቶች ጥራት ያለውና ምቹ የሆነ ንጽህና መጠበቂያ ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

4.3.3 ማህበራዊ ዋስትና

በማህበራዊ ዋስትና የስርዓታ-ጾታን እኩልነትና ተጠቃሚነትን በተመለከተ ኢትዮጵያ ተከታታይ የድህነት ቅነሳ መርሃግብሮችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ብታደርግም የተለያዩ እድሎችን የማያገኙ ድሆች እና አቅመ ደካሞች ቁጥር አሁንም ከፍተኛ ሲሆን ሴቶች አብዛኛውን ድርሻ መያዛቸው፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ለችግር የተጋለጡ ሴቶች፣ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ተፈጥሯዊና ሌሎች ምክንያቶች ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችና የተጎጂዎች ማህበራዊ ተደራሽነት ደረጃቸውን የጠበቀ አለመሆን፣ የበጀትና የህግ ማዕቀፎች ክፍተት፣ በማህበራዊ ዋስትና ስር የሚተገበሩ ፕሮግራሞች

ስርዓተ ፆታ ያማካሉ ቢሆንም በአግባቡ ተፈጻሚ አለመሆናቸው በማህበራዊ ዋስትና ዘርፍ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው። እነዚህንም ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- በገጠርና በከተማ የማህበራዊ ደህንነትንና ጥበቃ ፕሮግራሞች አካታች እንዲሆኑና የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን እንዲያረጋግጡ ይደረጋል፣
- ለአደጋ ተጋላጭና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ልዩ የማህበራዊ ዋስትና ድጋፍ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- የቤተሰብ የመልካም እሴት ግንባታና የእርስ በርስ የመረዳዳት ማህበራዊ ትስስርን ለማጠናከር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

4.3.4 መሰረተ- ልማት

በመሠረተ-ልማቶች ተደራሽነት ረገድ የንጹህ መጠጥ ውሃ እና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነት በበቂ ደረጃ ያለመስፋፋትና በገጠራማ አካባቢዎች የመንገድ እና የትራንስፖርት አገልግሎቶች ዕጥረት መኖር የጤናና የትምህርት ተደራሽነት ላይ እንቅፋት ፈጥሯል። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የዲጂታል፣ የኤሌክትሪክና የመንገድ መሰረተ ልማቶች ሥርዓተ-ጾታን ባገናዘበ መልኩ ምቹና ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

4.3.5 የሰላም ግንባታ

ግጭቶች በሚከሰቱበት ጊዜ ለሴቶች በቂ ጥበቃና ከለላ አለመደረጉ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ላይ የሴቶች ሚና አናሳ መሆን፣ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች ለሴቶች እኩል ተደራሽ አለመሆን፣ ሴቶች በሰላምና ደህንነት ተቋማት ውስጥ ያላቸው አነስተኛ የአመራር ውክልና፣ በሰላም ድርድሮችና ምክክሮች ላይ የሴቶች ተሳትፎ በበቂ ሁኔታ አለመረጋገጡ፣ በግጭት ውስጥ የተሳተፉ ሴቶች ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲቀላቀሉ በቂ ስራዎች አለመሰራታቸው፣ በድህረ-ግጭት ሥርዓተ ጾታን ያገናዘቡ የመልሶ ማቋቋም ስራዎች ውስንነት ያለባቸው መሆኑ ዋነኛ ችግሮች ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ሴቶች በሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት እንዲሁም ብሄራዊ ምክክር ሂደቶች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- ብሔራዊ የሴቶች የሰላምና ደህንነት የድርጊት መርሃ ግብር በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፣
- በግጭት ወቅት ለሴቶች ልዩ ጥበቃና ከለላ ለማድረግ እንዲሁም ያልተገደበ የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤
- በሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ምክንያት ለችግር የተጋለጡ ሴቶች ልዩ ድጋፍ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- ባህላዊና ሀገር በቀል የሰላምና የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ለስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ምላሽ እንዲሰጡ ይደረጋል፣
- በሰላምና ደህንነት ተቋማት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል።

4.4 ስርዓተ-ጾታ በአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢና ተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ

ለአየር ንብረት ለውጥ በይበልጥ ሴቶችና ህጻናት ተጋላጭ ከመሆናቸው በተጨማሪ ሴቶች በአካባቢ ጥበቃ አና በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት አናሳ መሆኑ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖውን ለመከላከልና ለመቋቋም የሚነደፉ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም የሚመደብ በጀት ስርዓተ ፆታን ግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑ ዋና ዋናዎቹ ችግሮች ሲሆኑ በአካባቢ እና በአየር ንብረት ስርዓተ ፆታን ለማስረፅና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሚከተሉት ዋና ዋና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ሴቶች በአየር ንብረት ለውጥ፣ በአካባቢ እና በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችና አስተዳደር መዋቅሮች ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖውን ለመከላከልና ለመቋቋም የሚነደፉ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም የሚመደብ በጀት ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረግ እንዲሆን ይደረጋል።

4.5 የሴቶችን የመሪነትና ውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎ ማሳደግ

ሴቶች በአመራርነት እና በውሳኔ ሰጭነት ቦታ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎች ቢኖሩም በየደረጃው ያለው ተሳትፏቸው ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር አሁንም ሰፊ ክፍተት መኖሩ፣ በህግ አውጭ፣ በህግ አስፈፃሚ፣ በህግ ተርጓሚ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሴቶችን የውሳኔ አሰጣጥ እና አመራር ሚና ላይ ክፍተቶች መኖራቸው፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ሴቶች በአባልነትና በአመራርነት ያላቸው ሚና ተገቢው ደረጃ ላይ አለመድረሱ፣ በሴቶች አመራርና ውሳኔ ሰጪነት ሚና ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶች አለመቀረፋቸው የሚስተዋሉ አንኳር ችግሮች ናቸው። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- ሴቶች በተደራጀ አግባብ ድምጻቸውን የሚያሰሙባቸውና ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት ሚና እንዲመጡ መሰረት የሚሆኗቸውን አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፤
- በሁሉም ሴክተሮች እና በየደረጃው ሴቶች ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት እንዲመጡ የሚያግዙ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤
- በፖለቲካዊ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሴቶችን ንቁ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ የሚያበረታቱ እርምጃዎች እንዲተገበሩ ይደረጋል፣
- የሴቶችን አመራርና ውሳኔ ሰጪነት ለማሳደግ በህግ ማዕቀፍ የተደገፉ አሰራር ስርዓት እና አዎንታዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
- የፖለቲካ ፓርቲዎች የሴቶችን ተሳትፎና አመራር እንዲያጎለብቱና በስርዓተ-ጾታ እኩልነት ግንባታ ድርሻቸውን እንዲወጡ የሚያስችሉ ስርዓቶች ይዘረጋሉ።

4.6 የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ተቋማዊነትን ማረጋገጥ እና የተጠያቂነት ስርዓትን ማጠናከር

በፌዴራልና በክልል ደረጃ አስፈጻሚ አካላት የስርዓተ-ፆታና ልዩ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ጉዳይን ከተቋማቸው ባህሪ በመነሳት አካቶ የመተግበር ክፍተት መኖሩ፣ ተቋማት የስርዓተ-ፆታ ጉዳይን በፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ እቅዶች እና ሪፖርቶች አካቶ ከመስራት አንጻር የአቅም፣

የግንዛቤና የቁርጠኝነት ውስንነት መኖሩ፣ የአካቶ ትግበራ ተጠያቂነት ሥርዓት አለመጠናከሩና አለመዘርጋቱ፣ ተቋማዊ አደረጃጀቱ ወጥ እና የተጠናከረ አለመሆኑ፣ ተቋማት የስርዓተ-ፆታ አዲት አከናውነው ያሉበትን ደረጃ አለመለየት የታዩ ችግሮች ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚያዘጋጇቸው እና የሚተገብሯቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች እና ሌሎች የአሰራር ስርዓቶች የሥርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማስፈን በሚያስችል መልኩ እንዲቀረጹና እንዲተገበሩ ይደረጋል፣
- የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ በሁሉም ሴክተሮች በአግባቡ ተካቶ እንዲሰራና ተቋማዊ እንዲሆን የሚያስችሉ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
- በፌዴራልና በክልል ደረጃ አስፈጻሚ አካላት የስርዓተ-ፆታ ጉዳይን ማካተት ተቋማዊነትን ለማረጋገጥ በየሶስት ዓመቱ የስርዓተ-ጾታ አዲት በማከናወን በግኝቶች መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይደረጋል፣
- በማንኛውም የፌዴራል የመንግስት መ/ቤትና የልማት ድርጅቶች የፖሊሲውን አፈጻጸም የሚከታተል አደረጃጀት በመ/ቤቱ ዋና የስራ ክፍሎች ደረጃ ተጠሪነቱ ቀጥታ ለተቋሙ የበላይ ሃላፊ የሆነ እና የማኔጅመንት አባል ሆኖ እንዲደራጅ ይደረጋል፣
- በሁሉም አስፈጻሚ አካላት የስርዓተ-ጾታን ጉዳይ ከማካተትና ተቋማዊነትን ከማረጋገጥ አኳያ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲተገበር ይደረጋል፣
- በፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች ቀረጻና ትግበራ ላይ የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ ለማካተት ልዩ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳታፊነታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

4.7. *ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከል*

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ስር ከሰደደና ከተዛባ የስርዓተ-ጾታ አመለካከትና ድርጊት የሚመነጭ በመሆኑ ለመከላከል ሊተገበሩ የሚገባቸው ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ወጥና ተመሳሳይ በሆነ መንገድ አለመዘጋጀታቸው፣ አሉታዊ ወጎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አለመቀረፋቸው፣ የህዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች በተለይም ትምህርት ቤቶች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ቦታዎች፣ የገበያና መዝናኛ ስፍራዎች፣

የስራ ቦታ እና የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች በሚፈለገው ደረጃ ከጥቃት ነጻ አለመሆናቸው፣ የመገኛኛ ብዙሃን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው መንገድ በተገቢው አለመስራታቸው፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚፈጸሙ ጥቃቶች እየተስፋፉ መምጣታቸው የመከላከል ስራው ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል። በመሆኑም በመከላከል ላይ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን የተዛባ የሥርዓተ ፆታ አመለካከቶች፣ ወጎች፣ ልምዶች፣ አስተሳሰቦችና ድርጊቶችን ለመቀየር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከል በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካታት ይደረጋል፣
- የህዝብ ማዝውተሪያ ስፍራዎች በተለይም ትምህርት ቤቶች፣ የትራንስፖርት ስፍራዎች፣ የገበያና መዝናኛ ስፍራዎች፣ የስራ ቦታ እና የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ከጥቃት ነጻ እንዲሆኑ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣
- የመገናኛ ብዙሃን ጥቃትን ለመከላከል ሚናቸውን እንዲወጡ እና ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት እንዲስፋፋ ለሚያደርጉ መገናኛ ብዙሃን የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶችን ለመከላከልና ድርጊቱን ፈጻሚዎች ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- ሁሉም ባለድርሻ አካላት ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከል የቅንጅት ሥራዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፤
- ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

4.8 ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ጥበቃና ምላሽ

ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶችና ወንዶች ልዩ ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርአት አለመኖሩ፣ ጥበቃ ማድረግ ኃላፊነት ለተሰጣቸው ተቋማት የተጠያቂነት ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ በህግ አስፈጻሚ አካላት የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ውስጥ ተካቶ በተገቢው መልኩ አለመተግበሩ፣ ለተጎጂዎች በተቀላጠፈ እና በተቀናጀ መልኩ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ ተጎጂዎችና ተፈናቃይ ሴቶች እና ህጻናት ተገቢው አገልግሎት አለመሰጠቱ፣ ተጎጂ ለሆኑ ሴቶች የመቋቋሚያና

የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች በሚፈለገው መልኩ አለመስፋፋት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊና የቅብብሎሽ አሰራር ስርዓቱ ወጥ አለመሆን፣ የህግ ክፍተትና የአፈፃፀም ችግር መኖሩ የጥበቃና ምላሽ አሰጣጥ ሥራው ውጤታማ እንዳይሆን ያደረጉ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና የጥበቃና ምላሽ ሥርዓቱን ለማጠናከር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ።

- ፆታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለመለየት የሚያግዝ ትንተና በማካሄድ ስጋትን የሚቀንስ ስትራቴጂያዊ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እንዲተገበር ይደረጋል፣
- በሁሉም ዓውዶች ጥበቃ ለማድረግና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ህጎች እንዲወጡ፣ እንዲሻሻሉ እና ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶችና ህጻናት ፍትህ እንዲያገኙ የሚያስችል ምቹ የህግ አገልግሎት ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- ጾታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ለተጎጂዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ እንዲሁም የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ጉዳይ አስተዳደርና አያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል።

5. የፖሊሲ ቁልፍ የውጤት መስኮች

በፖሊሰው የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎችንና እርምጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ የሚከተሉት ውጤቶች ይመዘገባሉ።

5.1 ከመብት ጥሰት የተጠበቁ ሴቶች

የሴቶችን መብትና ደህንነት የሚያስጠብቁ በአገሪቱ እውቅና የተሰጣቸው አለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶችን ተፈጻሚ በማድረግ፣ ለሴቶች መብት ምላሽ የሚሰጡ ሀገራዊ ህጎችንና የድርጊት መርሃ ግብሮችን በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ህጎች ለሴቶች መብት መከበር ትኩረት የሰጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ በሴቶች መብት ዙሪያ የተዛቡ አመለካቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የመብት ስርፀት ስራዎችን በመስራት፣ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙትን ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች የማይታገስ ማህበረሰብ በመፍጠር፣ ለሴቶች መብት ጥሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን ጉዳዮችና የህግ ክፍተቶች በመለየትና የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በማድረግ፣ የህግ አገልግሎት ፍትሃዊ ተደራሽነትን

በማረጋገጥ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ማደራጀት፣ መተንተንና መጠቀም ሥርዓት መዘርጋቱን በማረጋገጥ፣ በሴቶች መብት ላይ የሚሰሩ ተቋማትና አደረጃጀቶች እንዲጠናከሩ በማድረግ እንዲሁም ሴቶች መብቶቻቸውን ከማወቅ በተጨማሪ ያሉትን አገልግሎቶች መጠቀም እንዲችሉ መረጃ በማሰራጨት ሴቶችን ከመብት ጥሰት በመከላከል ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ይደረጋል።

5.2 በኢኮኖሚ ዘርፍ የተረጋገጠ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት

እኩል የኢኮኖሚያዊ እድሎችን በመፍጠር፣ አካታች የፋይናንስ ስርዓት በማጎልበት፣ በስራ ፈጠራ አስተሳሰብና ክህሎት መሰረታዊ ለውጥ በማምጣት፣ ለሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም የሚያሳድጉና የሚያበረታቱ የህግና የፖሊሲ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በማድረግ፣ በሁሉም ደረጃ የኢኮኖሚ መስኮች ሴቶችና ወንዶች እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ በንግድ፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በቴክኖሎጂ፣ በግብርናና በአገልግሎት ዘርፎች የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነት በማረጋገጥ፣ የሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነት፣ እንዲሁም የንብረት ባለቤትነት፣ ማስተዳደር፣ ማስተላለፍና የተጠቃሚነት መብት በማረጋገጥ፣ ክፍያ የማይፈፀምባቸው የእንክብካቤ እና የቤት ውስጥ ስራዎች እውቅና እንዲያገኙና ፍትሃዊ የስራ ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ እንዲሁም የስራ ጫና ሊቀንሱ የሚችሉ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ በማድረግ ሴቶች በኢኮኖሚው መስክ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በሃገር ኢኮኖሚ ልማት ጉልህ ድርሻ እንዲኖራቸው ከዚህ ፖሊሲ የሚጠበቅ ውጤት ነው።

5.3 በማህበራዊ ዘርፍ የተረጋገጥ የስርዓታ-ጾታ እኩልነትና ፍትሐዊነት

በሴቶችና ወንዶች መካከል ያለውን የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ዙሪያ ያሉ ክፍተቶች ለመፍታት የሚያስችል አካታች ስርዓተ-ትምህርት እና የትምህርት የልማት ፕሮግራም እንዲዘረጋ በማድረግ፣ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶች በማሟላት ለሴቶችና ታዳጊዎች ምቹ የትምህርት አካባቢ በመፍጠር፣ አዎንታዊ ድጋፎችን በመተግበር፣ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሚታየውን የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ልዩነት በማጥበብና የሴት ተማሪዎችን የትምህርት እድል በማስፋፋት በትምህርት ሴክተር የስርዓተ-ጾታ እኩልነት ማረጋገጥና የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ ለስርዓተ-ጾታ እኩልነት አካታች የጤና ልማት ፕሮግራም በማጠናከር፣ የሴቶችንና የታዳጊዎችን የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ የመረጃና አገልግሎቶች ተደራሽነት በማሳደግ እንዲሁም ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ሴቶችና ታዳጊዎች ህክምና የሚያገኙበትን ስርዓት በማጠናከር በጤናው ዘርፍ የስርዓተ-ጾታ አኩልነትን ማረጋገጥ ከዚህ ፖሊሲ

የሚጠበቅ ውጤት ነው። በተጨማሪም ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ የማህበራዊ ዋስትና የልማት ፕሮግራም በመንደፍ፣ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን ማዕከል ያደረገ ልዩ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት በመተግበር፣ በገጠርና በከተማ ስርዓተ-ጾታ ተኮር የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶችን በማስፋፋት፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የመንገድ እና የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋትና ተደራሽነታቸውን በማረጋገጥ የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ማስፈን ይጠበቃል። ሴቶችና ታዳጊዎች በሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ፣ ሀገራዊ የሴቶች ሰላምና ደህንነት የድርጊት መርሃግብርና የሽግግር ፍትህን በመተግበር፣ በግጭት ወቅት ለሴቶች ልዩ ጥበቃና ከለላ ስርዓትን በመተግበር፣ ባህላዊና ሀገር በቀል የሰላምና የግጭት አፈታት ለስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ምላሽ እንዲሰጥ በማድረግ፤ በሰላም ግንባታና ሰላም ማስከበር የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ እንዲሁም ለሴቶች የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን በማቅረብ በሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት የስርዓተ-ጾታ እኩልነት እንዲሰፍን የሚጠበቅ ውጤት ነው።

5.4 በአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት የተረጋገጠ የስርዓተ-ጾታ እኩልነት

ሴቶች በአየር ንብረት ለውጥ፣ በአካባቢ እና በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎና የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን በማሳደግ፣ በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባት የሴቶችን ተጠቃሚነት በማሳደግ እና ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን በመንደፍና በጀት በመመደብ የአየር ንብረት በሴቶች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መቀነስና በአካባቢ ጥበቃና ልማት የሴቶችንና የወንዶችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ከዚህ ፖሊሲ የሚጠበቅ ውጤት ነው።

5.5 ያደገ የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት፣ ተሳትፎና ውክልና

በሁሉም ዘርፎች የውሳኔ ሰጪነት እና የመሪነት ሚና ላይ የሴቶች እና የወንዶችን እኩል ተሳትፎና ውክልና በማረጋገጥ፣ የሴቶች ውክልና በየደረጃው ባሉ የአመራርና ውሳኔ ሰጭነት ቦታዎች ከወንዶች ጋር ለማመጣጠን የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመተግበር፣ በሴቶች አመራርነትና ውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎ ዙሪያ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን በመተግበር፣ ለሴቶች የአመራር እና ውሳኔ ሰጪነት ማብቃት ግልጽ እና ከአድልዎ ነፃ የሆነ የምልመላ ስርዓት በመዘርጋት እንዲሁም ለሴቶች

አመራርነት ምቹ የሆነ አካባቢ በመፍጠር የሴቶች የአመራርነትና ውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎና ሚና ማሳደግ የሚጠበቅ ውጤት ነው።

5.6 የጎለበተ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ተቋማዊነት

የሚዘጋጁ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችና የአሰራር ሥርዓቶች ሥርዓተ ጾታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ በማድረግ፣ በሁሉም ዘርፎች የሥርዓተ ጾታ ማካተትን ተቋማዊ በማድረግ፣ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ማካተት ተቋማዊነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ የሥርዓተ ጾታ አዲትና የሥርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም የስርዓተ-ጾታ ማካተት የተጠያቂነት ሥርዓትን በመተግበር የሥርዓተ ጾታ እኩልነት እና የሴቶች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት መረጋገጥ የሚጠበቅ ውጤት ነው።

5.7 ጥቃትን የማይታገስ ማህበረሰብ

ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን የሚያበረታቱና በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን የተዛባ የሥርዓተ ፆታ አመለካከት፣ ልምዶችና ወጎች ለመቀየር የሚያስችሉ ስልቶችን በመተግበር፣ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን በመተግበር፣ የህዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች በተለይም ትምህርት ቤቶች፣ የገበያና መዝናኛ ስፍራዎች፣ የስራ ቦታ እና የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ከጥቃት ነጻ እና ምቹ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የመገናኛ ብዙሃን ለጾታዊ ጥቃት መከላከል ሚናቸውን በማጉላት፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በመቆጣጠር እንዲሁም የሁሉንም አቅም፣ ሀብት፣ ዕውቀትና ክህሎት በማቀናጀት ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን የማይታገስ ማህበረሰብ መፍጠር የዚህ ፖሊሲ ውጤት ነው።

5.8 ፆታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች የተደረገ ጥበቃና ምላሽ

ፆታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ልየታና ትንተና በማካሄድ፣ በሁሉም ዓውዶች ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተጋላጭና ተጎጂዎች በተመለከተ ህጎች እንዲወጡና እንዲሻሻሉ በማድረግ፣ የፍትህ አካላትን አቅም በማጎልበት ጥቃት ፈፃሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ፣ በህግ አስከባሪ አካላት በመደበኛ የስልጠና እና የስርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት በማድረግ፣ ተጎጂዎች በፍትህ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ለተደጋጋሚ የስነ-ልቦና ጉዳት እንዳይዳረጉ የተቀናጀ የጤና፣ የፍትሕ፣ የስነልቦናና የማህበራዊ አገልግሎቶች በማጠናከርና ተደራሽ በማድረግ፣ ለተጎጂዎች ምቹ ችሎቶች፣ ልዩ የምርመራና የዓቃቤ ህግ አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ በማድረግ፣ ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ

ጊዜያዊ መጠለያ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች እና ተሐድሶ ማዕከላት አገልግሎቶችን በማስፋፋት፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ሴቶች እና ህጻናት ልዩ ትኩረት የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን በመንደፍና በመተግበር፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ጉዳይ አስተዳደርና አያያዝ ማዕቅፍ በመተግበር እና ለጾታዊ ጥቃት ተጎጂዎችና ተጋላጮች አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የአሰራር ሥርዓቶችን በመተግበር የተጠናከረ ጥበቃና የህግ ከለላ መፍጠር የሚጠበቅ ውጤት ነው።

6. **የፖሊሲ ማውጣት ስልጣንና የፖሊሲውን ተፈጻሚነት ወሰን**

ፖሊሲውን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚያስፈጽምሲሆንኢትዮጵያ ውስጥ በሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በፌደራልና በክልሎች ተፈፃሚ ይደረጋል።

7. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

7.1 የተቋማት ተግባራትናሃላፊነት

የመንግስት ተቋማት፡- ፖሊሲውን ለማስፈጸም በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ ሁሉም አስፈጻሚ አካላት ማንኛውም የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ስትራቴጂዎችና የልማት ዕቅዶች የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ፣ ለዚህም በቂ በጀት የመመደብ የመተግበር ግዴታ አለባቸው። በየደረጃው ያሉ ተቋማት ከፌዴራል እስከ ታችኛው የመንግሥት መዋቅር ድረስ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አደረጃጀቶችን የመዘርጋት፣ የሴቶችን የአመራርነትና የውሳኔ ሰጭነት ሚና የማሳደግ፣ ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን የመከላከል፣ ሕጋዊ ጥበቃ የማድረግና ምላሽ የመስጠት እንዲሁም የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል።

ዓለም አቀፍ ተቋማትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡- የስርዓተ-ፆታ እኩልነት እና ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ዙሪያ ለሚሰሩ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ፣ ስርዓተ-ጾታ እኩልነት እና ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ረገድ ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር በመስራት፣ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት እና ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት በተመለከተ የጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሰሩ ድጋፍ በማድረግ ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ።

የግል ዘርፎች፡- የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈንና ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የክህሎት ስልጠና በመስጠት፣ በየደረጃው የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አደረጃጀቶችን የመዘርጋት፣ የስራ ዕድል በመፍጠርና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን በመወጣት፣ ፆታ መሠረት ያደረገ ጥቃትን የማይታገስ ምቹ የስራ ቦታ ለመፍጠር የሚያስችል ውስጣዊ የአሰራር ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ።

7.2 የፖሊሲው ማስፈፀምያ የህግ ማዕቀፎች

ይህንን ፖሊሲ በአግባቡ በሥራ ላይ ለማዋልና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት እንዲቻል፣ በሥራ ላይ ያሉ የሕግ ማዕቀፎች ከሴቶች መብት ማስጠበቅ፣ ሥርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ ከጥቃት መከላከልና ምላሽ አኳያ በጥናት በመለየት እንዲሻሻሉ ይደረጋል።

የተጠቃለለ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መከላከልና ምላሽ መስጠት የሚያስችል ህግ፣ በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸሙ ፆታዊ ጥቃቶች ለመከላከል የሚያስችል ደንብ፣ የስርዓተ-ጾታ እኩልነት አተገባበርና የተጠያቂነት ደንብ እንዲወጡ ይደረጋል።

ከዚህ በተጨማሪ የፖሊሲውን መርሆዎች ተፈጻሚ ለማድረግና ለሚያጋጥሙ አዳዲስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶች ተገቢውን ሕጋዊ ምላሽ ለመስጠት ወደፊት በሚካሄዱ ጥናቶችና የምርምር ግኝቶች ላይ ተመስርቶ አዳዲስ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲረቀቁና በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ይህም የአሠራር ሥርዓቶችን ለማዘመን፣ ተጠያቂነትን ለማስፈንና የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ በሕግ ለመደገፍ የሚያስችል ተለዋዋጭና ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ያስችላል።

7.3 ፕሮግራሞችና ንዑስ ፕሮግራሞች

የሴቶች መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። በዚህ ፕሮግራም ስር የሴቶች መብት ስርጸት፣ ግንዛቤና ንቅናቄ ንዑስ ፕሮግራም፣ በሴቶች መብት ላይ የሚሰሩ የሴት አደረጃጀቶች የማጠናከር ንዑስ ፕሮግራም፣ የነጻ የህግ አገልግሎትና ድጋፍ ንዑስ ፕሮግራም ተግባራዊ

የሚደረጉ ሲሆኑ በዚህም የጥቃት መከላከል ስትራቴጂ የመንደፍና የመተግበር፣ የማህበረሰብን ተሳትፎ ሊያረጋገጥ የሚችሉ ስልቶችን የመቀየስ፣ አደረጃጀቶችን በቴክኒክና በማቴሪያል ድጋፍ የማጠናከር፣ ነጻ የህግ ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን የማስፋፋትና አቅም የማጎልበት ስራዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል።

በኢኮኖሚ ዘርፍ የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የኢኮኖሚያዊ እኩል ተጠቃሚነት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ፕሮግራም ስር፣ የሴቶች የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች የማጠናከር ንዑስ ፕሮግራም፣ የሴቶች የፋይናንስ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ንዑስ ፕሮግራም፣ በግብርና ዘርፍ የሴቶች ተጠቃሚነት ማሳደግ ንዑስ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆኑ የሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነትና የንብረት ባለቤትነት የማረጋገጥ፣ የግንዛቤ ሥራዎችን የመስራት፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችንና የህጻናት ማቆያዎችን የማስፋፋት፣ ለሴቶች ምቹ የሆነ የግብርና ኤክስቴንሽንና ግብዓቶችን ተደራሽ የማድረግ፣ ለኢንተርፕራይዝ አንቃሳቃሽ ሴቶች የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፎችን የማድረግ እና ለሴቶች አመቺ የሆኑ የፋይናንስ አገልግሎቶችን የማስፋፋት ሥራዎች የሚተገበሩ ይሆናሉ።

በማህበራዊ ዘርፍ የስርዓታ-ጾታ እኩልነትና ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ የማህበራዊ አገልግሎቶች እኩል ተጠቃሚነት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ፕሮግራም ስር በትምህርት ዘርፍ የሥርዓት ጾታ እኩልነት ማረጋገጥ ንዑስ ፕሮግራም፣ የሴቶች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተሳትፎ ማስፋፊያ ንዑስ ፕሮግራም፣ በጤና ዘርፍ የሥርዓት ጾታ እኩልነት ማረጋገጥ ንዑስ ፕሮግራም፣ የሴቶችና ሥርዓተ ምግብ ንዑስ ፕሮግራም፣ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት ማስፋፋት ንዑስ ፕሮግራም፣ የሴቶች በመሰረተ ልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ንዑስ ፕሮግራም፣ የሴቶች ሰላምና ደህንነት ግምባታ ንዑስ ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋሉ። ለዚህም አካታችና ምቹ የትምህርት አካባቢ የመፍጠር፣ በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ተፈፃሚነት ማረጋገጥ፣ ለሴቶች የልዩ አዎንታዊ ድጋፍ እርምጃ ተግባራዊ የማድረግ፣ በትምህርት ዘርፍ የማበረታቻ ስርዓት የመዘርጋት፣ ጥራቱን የጠበቀ የጤናና የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ የማድረግ፣ለሴቶችና ታዳጊ ሴቶች የንፅህና መጠበቂያ አቅርቦት ተደራሽነት ላይ መስራት፣ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የመከላከል፣ በስርዓተ ምግብና ስርዓተ-ጾታ ዙሪያ የግንዛቤ ስራ የመስራት፣ ሴቶች በማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ፣ የመሰረተ ልማት ፕሮግራሞች ስርዓተ-ጾታን ያማከሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም ሴቶች በሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት ላይ ተሳትፏቸውና የአመራር ሚናቸው የሚያሳድጉ ተግባራት የሚተገበሩ ይሆናሉ።

በአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ የስርዓተ-ጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የአካባቢ ጥበቃና ስርዓተ-ጾታ ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ፕሮግራም ስር በአየር ንብረት ለውጥ፣ በተፈጥሮ ሃብትና በአካባቢ ጥበቃ የሴቶች ተሳትፎ ማስፋፊያ ንዑስ ፕሮግራም እና በአየር ንብረት ለውጥ፣ በተፈጥሮ ሃብትና በአካባቢ ጥበቃ የሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ንዑስ ፕሮግራም የሚተገበሩ ሲሆን የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራሞች ስርዓተ-ጾታን ያማከሉ ሆነው እንዲተገበሩ የማድረግ፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችና የአስተዳደር መዋቅሮች ውስጥ የሴቶች እኩል ተሳትፎን የማረጋገጥ፣ ለአረንጓዴ ልማት ከሚመደቡ በጀቶች ሴቶችን ፍትሐዊ ተጠቃሚ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራዎች የሚተገበሩ ይሆናሉ።

የሴቶችን መሪነትና የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሴቶች አመራርና ውሳኔ ሰጭነት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። ይህን ፕሮግራም ለማሳካት የሴቶችን የአመራርና ውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎ ማጎልበት ንዑስ ፕሮግራም፣ የሜንተርሽፕ እና ኮቺንግ ንዑስ ፕሮግራም እና የአዎንታዊ ድጋፍ እርምጃዎች ንዑስ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆኑ ለዚህም የሴቶች የአመራርና ውሳኔ ሰጪነት ስልጠና ካሪኩለም የመቅረጽና የመተግበር፣ የአመራር ሴቶች ቁትን የማጠናከር፣ የወንዶችን ተሳትፎ የማጎልበት፣ የእውቅናና የማበረታቻ ስርዓት የመዘርጋት እና የሴቶችን እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አዎንታዊ የድጋፍ እርምጃዎች በህግ ማዕቀፍ የማካተትና የመተግበር ስራዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ተቋማዊነትን ለማረጋገጥ የስርዓተ-ጾታ አካቶ ትግባራ የተጠያቂነት ስርዓት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ፕሮግራም ስር የስርዓተ-ጾታ ማካተት ተቋማዊነት የተጠያቂነት ንዑስ ፕሮግራም፣ የአቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም እና የስርዓተ ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ንዑስ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆኑ የስርዓተ-ጾታ ተቋማዊነት ክትትልና ግምገማ ስርዓት የመዘርጋት፣ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ ዕቅዶችና ሪፖርቶች ስርዓተ-ጾታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ለማስቻል የተጠያቂነት ማዕቀፍ የማዘጋጀትና የመተግበር፣ የትብብርና ቅንጅት አሰራሮችን የመዘርጋት፣ የመረጃ አያያዝና የሪፖርት ስርዓት የማጠናከር፣ የሰው ሀብት አቅም የማጎልበት እንዲሁም የሚመደቡ በጀቶች ለስርዓተ-ጾታ ምላሽ የሚሰጡ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች የሚሰሩ ይሆናሉ።

ጥቃትን የማይታገስ ማህበረሰብ ለመፍጠር ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን መከላከል ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ፕሮግራም ስር የተዛቡ ስርዓተ-ጾታ አመለካከቶችና ማህበራዊ ወጎች የመቀየር

ንዑስ ፕሮግራም፣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ጉዳይ አያያዝ ንዑስ ፕሮግራሞች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆኑ በአዎንታዊ የማህበረሰብ እሴቶች ዙሪያ መልካም ተሞክሮ የመቀመርና የማስፋፋት፣ የወንዶች አጋርነትን የማጠናከር፣ የማህበረሰብ ንቅናቄ የመፍጠር እና የታዳጊ ሴቶችና የቤተሰብን አቅም የመገንባት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናሉ።

ፆታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ጥበቃና ምላሽን ለማረጋገጥ የጥቃት ተጎጂዎች ጥበቃ፣ ከለላና ምላሽ ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የተጎጂዎች ጥበቃና ከለላ ንዑስ ፕሮግራም እና ለፆታዊ ጥቃት ተጎጂዎች የተሃድሶ እና መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ንዑስ ፕሮግራሞች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችና የቅብብሎሽ አሰራሮች የማጠናከር፣ ለፆታዊ ጥቃት ተጎጂዎች ጥራት ያለውና ተደራሽ አገልግሎት የመስጠት፣ የህግ ማሻሻያና የአድቮኬሲ ስራ የመስራት፣ የህዝብ ማዘውተሪያ እና አገልግሎት መስጫዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ የማድረግ፣ በሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች የፆታዊ ጥቃት ጥበቃ ሥራዎችን የማጠናከር ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናሉ።

7.4 የፖሊሲው አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ

ይህ የብሔራዊ የሴቶች ማብቃት እና ስርዓተ-ፆታ እኩልነት ፖሊሲ አተገባበር በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉትንና የተዛቡ አመለካከቶች ከመቅረፍ፣ ለሴቶች ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ከመፍጠር፣ መዋቅራዊ አደረጃጀቶችንና ቅንጅታዊ አሰራሮችን ከማጠናከርና ጥቃትን የሚጠየፍ ማህበረሰብ ከመፍጠር እና በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ መስኮች የሴቶችንና የወንዶችን እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ያስገኘውን ውጤት በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ይደረግበታል። የክትትልና ድጋፍ ሥራው ፖሊሲውን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ የማስፈፀሚያ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ይህም የፖሊሲ ቁልፍ የውጤት መስኮች ለማሳካትና መሳካታቸውንና ወቅታዊ እርምጃዎች መወሰዳቸውን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የፖሊሲ ክለሳ ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ለማረጋገጥ ያስችላል። በመሆኑም ይህን የብሔራዊ የሴቶች ማብቃት እና የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ፖሊሲ ለመተግበር የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

- የዚህን ፖሊሲ አፈጻጸሙን ለመከታተልና ለመገምገም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዋነኝነት የሚመራው ሆኖ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሴክሬታሪያትነት የሚያገለግልበት ሁሉንም ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያቀፈ አደረጃጀት ይኖረዋል፣

- ከፈደራል እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የፖሊሲውን አፈጻጸም ለመከታተልና ውጤት ለመለካት የሚያስችል ወጥ የሆነ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፣
- ፖሊሲው ሴቶችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግና የስርዓተ-ጾታ እኩልነት ለማረጋገጥ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መተግበሩን በመስክ በመገኘት ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ ወጥ የሆነና ውጤትን ለመለካት የሚያስችል የመስክ ክትትል ቼክሊስት በማዘጋጀት ሁሉንም አካላት ያካተተ የባለሙያዎች ቡድን በማቋቋም በዓመት አንድ ጊዜ የመስክ ክትትል ይደረጋል፣ ውጤቱም ለሚመለከታቸው አካላት የሚቀርብ ይሆናል፣
- ወቅቱን ጠብቀው በሚላኩ ሪፖርቶች፣ በመስክ ከሚደረገው የፖሊሲውን አፈጻጸም ክትትል ጎን ለጎን የፌደራልና የክልል አስፈጻሚ አካላትና የሴት አደረጃጀቶች እንዲሁም የልማት አጋሮች የሚሳተፉበት የጋራ መድረክ በዓመት አንድ ጊዜ በማካሄድ የፖሊሲው አፈጻጸም በጋራ ይገመገማል። የግምገማውን ውጤት ተከትሎ የጋራ አቅጣጫ በማስቀመጥ ፖሊሲው ይበልጥ ተፈጻሚ እንዲሆን ይደረጋል። በተጨማሪም የአፈፃፀም የፅሑፍ ሪፖርቱ፣ በመስክ የታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖች እና በፊት ለፊት ግምገማ ወቅት የተለዩ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የዕቅድ አፈጻጸም የደረሰበትን ደረጃ የሚያሳይና የተጠያቂነት አሰራርን የሚያረጋግጥ ችግር ፈቺና ተሞክሮን የሚያሳይ የጽሁፍ ግብረ-መልስ በመስጠትና ደረጃቸውን በማሳወቅ የቀጣይ አፈጻጸማቸው እንዲያሳድጉ ይደረጋል፣
- በየሶስት ዓመቱ የብሔራዊ የሴቶች ማብቃት እና የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ፖሊሲው ያመጣውን ውጤት በመካከለኛ ዘመን ግምገማ በማድረግ ለቀጣይ ሥራዎች መሻሻል በግብዓትነት እንዲውሉ ይደረጋል። ይህ ግምገማ ከባለድርሻ አካላትና ማህበረሰቦች አካታች በሆነ መረጃ የማሰባሰብ ዘዴ እንዲሁም በተለያዩ አገራዊና አለም አቀፋዊ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን መሠረት አድርጎ ይከናወናል፣
- ሪፖርት ማቅረቢያ መንገዶችን መዘርጋት ፖሊሲውን ለማስፈጸም ወሳኝ ነው። ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግስት ተቋማት ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚወስዷቸው እርምጃዎች ጋር በተያያዘ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማስቀመጥና የማካፈል እንዲሁም በራሳቸውና በሚከታተሏዋቸው ሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የተወሰዱ እርምጃዎች እና የተሰጡ አገልግሎቶች በሚመለከት በሚኒስቴሮች ም/ቤት በበላይነት ለሚመራው የሴክተር አስተባባሪ አካልና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለማቅረብ ቁርጠኛ ሊሆኑ ይገባል፣

- ፖሊሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥናት ላይ ተመሥርቶ ተሞክሮዎችን ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል።

8.ተዛማጅ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንብ እና ስምምነቶች

በብሄራዊ የሴቶች ማብቃትና ሥርዓተ ጾታ እኩልነት ፖሊሲ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው።

8.1 የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች እና የመሰረተ ልማት ፖሊሲዎች

የግብርና ፖሊሲ በግብርና ዘርፍ ያሉ የመሬት ተጠቃሚነት፣ የግብርና ግብዓት፣ የኤክስቴንሽንና ሌሎች አገልግሎቶች ሴቶችና ወንዶችን በእኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንደሚያደርግ ይጠበቃል። የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ የአየር ንብረት ለውጥ በሴቶችና በወንዶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለይቶ በማስቀመጥ፣ ሴቶች በአካባቢ ጥበቃ ላይ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ ከአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራሞችና ለዚህ አላማ ከሚውለው ሀብት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ፣ ሴቶችና ወንዶች ከኢንዱስትሪ ልማት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች በማስወግድና ተሳትፎዎችን ለማሳድግ የማበረታቻ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ይጠበቃል። የንግድ ፖሊሲ፣ ሴቶችና ወንዶች በንግዱ ዘርፍ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ፣ በንግድ ላይ የተሰማሩ ሴቶች የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች በማስወግድና ተሳትፎዎችን ለማሳድግ የማበረታቻ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ይጠበቃል። ብሔራዊ የውሃ፣ ኢነርጂና ማእድን ፖሊሲዎች፣ በየዘርፎቹ የሚሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች ለሴቶችና ለወንዶች ተደራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ ሴቶች በዘርፎቹ ውስጥ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሚና አላቸው። የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030" ፖሊሲ በመላ ሀገሪቱ ዲጂታል መሰረተ ልማትንና የኢንተርኔት ተደራሽነትን በማስፋፋት፣ የሞባይልና የብሮድባንድ ግንኙነትን በማሳደግ፣ ጾታን ሳይለይ ሁሉም ሰዎች የዲጂታል አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል። እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች ፖሊሲውን ለማስፈፀም አጋዥ ሆነው ያገለግላሉ።

8.2 የማህበራዊና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች

የጤና ፖሊሲ የጤና ተቋማትና አገልግሎቶችን (በተለይ የስነ ተዋልዶ ጤና፣ የቅድመና ድህረ ወሊድ አገልግሎት) በማስፋፋት፣ ለሴቶች ተደራሽና ተስማሚ እንዲሆኑ በማረጋገጥና የጤና ዘርፉ የስርዓተ ፆታ

እኩልነትን ማስፈኑን ያረጋግጣል። ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ተገቢውን የህክምናና ሁሉን አቀፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ያመቻቻል። የትምህርት ፖሊሲ፣ የትምህርት ዘርፍ ሙሉ ለሙሉ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን እንዲያሰፍን፣ የትምህርት ተቋማት ለሴቶች ምቹ እንዲሆኑና ከፆታዊ ጥቃት ነፃ እንዲሆኑ በማድረግ አስተዋፅኦ ያደርጋል። የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ፣ ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች ተገቢውን ማህበራዊ ከለላና አገልግሎት እንዲያገኙ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ለስርዓተ ፆታ እኩልነት ምላሽ የሚሰጡ እንዲሆኑ ያደርጋል። የምግብና አመጋገብ ስርዓት ፖሊሲ፣ ሴቶች በተለይም ታዳጊ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የተዛቡ አመለካከቶች ምክንያት የሚገጥማቸውን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት ፖሊሲውን ስርዓተ ፆታን ባማከለ መልኩ በመተግበር የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ያስችላል። የህጻናት ፖሊሲ፣ የቀዳማይ ልጅነት ፖሊሲ፣ የህጻናትን መብት በማስጠበቅና ሁሉም እርምጃዎች የህጻናትን ደህንነት ግምት እንዲገባ በማድረግ ለሴት ህጻናት ከለላ ያደርጋል፣ ተሳትፎቸውን ያረጋግጣል።የወጣቶች ፖሊሲ፣ ወጣት ሴቶች በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ዘርፎች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች ፖሊሲውን ለማስፈፀም አጋዥ ሆነው ያገለግላሉ።

8.3 የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ሴቶች በዘርፉ የበለጠ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እርምጃዎችን በማስቀምጥ፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለሴቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል። እንዲሁም ሌሎችተዛማጅ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች ፖሊሲውን ለማስፈፀም አጋዥ ሆነው ያገለግላሉ።

8.4 የፍትህ አስተዳደር ፖሊሲዎች፡-

የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲና የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ስርዓተ-ፆታን ባማከለ መልኩ በመተግበር፣ የመብት ጥሰትና ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ተገቢውን ፍትህና ነፃ የህግ ድጋፍን ጨምሮ የተለየ ከለላ እንዲሰጣቸው ያደርጋል። ኢትዮጵያ ፈርማና አጽድቃ የሀገሪቱ የህግ አካል ያደረጋቻቸው አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች ለአብነት የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ቻርተር፣ የአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ

መብቶች ቃል ኪዳን (ICCPR)፣ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሁሉንም አይነት መድሎዎች ለማስወገድ ስምምነት (CEDAW)፣ አለም አቀፍ የዘር መድልዎ (ICERD)፣አለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የባህል መብቶች ቃል ኪዳን (ICESCR) ፣ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን (CRC)፣ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን (CRPD) ፣ የአፍሪካ የሰብአዊ እና ህዝቦች መብቶች ቻርተር ፣ ለአፍሪካ የሰብአዊ እና ህዝቦች መብት በአፍሪካ የሴቶች መብት ቻርተር (ማፑቶ ፕሮቶኮል) ፣የአፍሪካ የአረጋውያን መብቶች ቻርተር ፕሮቶኮል፣ በአፍሪካ ውስጥ የተፈናቀሉ ዜጎችን ለመከላከልና ለመርዳት የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላ ኮንቬንሽን) ፣ የአፍሪካ የዲሞክራሲ፣ የምርጫ እና የአስተዳደር ቻርተር እና ሌሎች ስምምነቶችና ድንጋጌዎች ፖሊሲውን ለማስፈፀም አጋዥ ሆነው ያገለግላሉ።

9.የቃላት ፍቺ

ጾታ (Sex)፡ በተፈጥሮ የሚገኝ፣ በመወለድ የሚመጣ፣ የማይለወጥ፣ በሁሉም ስፍራ አንድ የሆነና ሰዎች ሴት ወይም ወንድ በሚል የሚመደቡበት ተፈጥሮአዊ ምድብ ነው።

ስርዓተ-ጾታ (Gender)፡ ከማህበረሰብ የምንማረው፣ በሃገር፣ በማህበረሰብ፣ በቤተሰብ፣ በግለሰብ ደረጃ ሊለያይ የሚችል፣ በጊዜ ሒደት የሚለዋወጥ፣ ሆን ተብሎ ወይም በዘፈቀደ የተፈጠሩ የወንዶችና የሴቶች ሚናና ተያያዥ ጉዳዮች የሚንጸባረቁበት ነው።

የሥርዓተ ፆታ ግንኙነቶች (Gender Relations)፡ ይህ ግንኙነት በዋናነት በወንዶችና ሴቶች መካከል ያለውን የኃይል ሚዛን የሚያመለክት ሲሆን በሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ በአብዛኛው ለወንዶች ያደላ ሲሆን በአንጻሩ ሴቶች በማህበረሰቡ ከሚጠብቅባቸው ባህሪያ ለየት ካሉ ተቀባይነት ከማጣቸውም በላይ ይወገዛሉ።

የሥርዓተ ፆታ ጅምላ ፍረጃ (Gender Stereotypes): የሥርዓተ ፆታ ጅምላ ፍረጃ ሰዎች በፆታቸው መሰረት በምን መልኩ ባህሪያቸው ሊገነባ እንደሚገባው ቅድመ ግምት የማስቀመጥ ሂደት ነው። የጅምላ ፍረጃው ሰዎች ስለወንዶች እና ስለ ሴቶች ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው እና ሁለቱም ፆታዎች የመረጡትን አይነት አኗኗር እንዳይከተሉ የሚገድብ ነው።

ሥርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ መድልዎ (gender based discrimination)፡ ሥርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ መድልዎ ማለት ሰዎች በፆታቸው ምክንያት የሚፈጸም የማግለል እና ባልተገባ ወይም ከህግ ውጪ ልዩ ጥቅም የመስጠት ወይም የመከልከል ተግባር ሲሆን ይህም በስራ ቅጥር፣ በዕድገት፣ በዝውውር፣ በትምህርት ዕድል እና በሌላ የእድገት እድሎች ላይ ሴቶች እኩል እንዳይታዩ የሚያደርግ ነው።

የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት (gender disparity)- በሴቶች እና በወንዶች መካከል በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና፣ ባህላዊ መስኮች ዙሪያ በተሳትፎና በተጠቃሚነት፣እድሎችና ተደራሽነት በተመለከተ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ነው።

የሥርዓተ ፆታ ምላሽ ሰጪነት (gender responsiveness)፡ ተለይተው የተመለከቱ የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮችን የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን በሚያረጋግጥ አግባብ የማቀድና የማስፈጸም ተግባር ሲሆን በህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ በስትራቴጂዎች፣ በበጀት፣ በስልጠናና እና በዕቅድ ላይ ምላሽ ሰጪ የሆነ የሥርዓተ ፆታ አካሔድን መከተል ነው።

ሥርዓተ-ፆታን ማካተት (gender mainstreaming) ፡ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ እቅዶች እና ሌሎች እርምጃዎች ሂደት ውስጥ የሴቶችና የወንዶችን/ስርዓተ ፆታ/ጉዳዮችን ሁኔታና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት መተግበር ነው።በተጨማሪም የሚወሰዱ እርምጃዎች ከስርዓተ ፆታ እኩልነት አኳያ ፋይዳና ውጤቱን ማሳየትን ያካትታል።

የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት (gender audit)፡- የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና የሴቶችን የማብቃት ኃላፊነት፣ እሴት እና ፖሊሲ ላይ ተጠያቂነትን የሚገመግም ሂደት ነው። ተቋማት በሥርዓተ-ፆታ ላይ የገቡትን ቁርጠኝነት ለማሳካት በተሰጣቸው ኃላፊነት፣ እሴታቸው እና ራዕያቸው ላይ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና አፈጻጸም ለማሻሻል የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል።

የሥርዓተ-ፆታ ትንተና (gender analysis)፡- የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የሴቶችና የወንዶችን የተለያዩ ፍላጎቶች እና ስጋቶች በተመለከተ መረጃን የመሰብሰብ እና የመተንተን ዘዴ ነው። እንቅፋቶችን ለመፍታት የታሰቡ ፖሊሲዎችና እርምጃዎች በሴቶችና ወንዶች ላይ ያላቸውን ተፅእኖ በመገምገም ሴቶች እና ወንዶች፣ ልጃገረዶች እና ወንዶች ልጆች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ መንገድ ይከፍታል።

በጾታ የተከፋፈለ መረጃ (sex disaggregated data)፡ በሴቶች እና በወንዶች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ መጠናዊ ስታቲስቲካዊ መረጃ ነው።

ተግባራዊ የሥርዓተ-ፆታ ፍላጎቶች (practical gender needs)፡ በሴቶች እና በወንዶች ተለይተው የሚታወቁ ፍላጎቶች ሲሆኑ ከልማዳዊ የፆታ የስራ ክፍፍል የሚነሱ ናቸው። እንደ የውሃ አቅርቦት፣ የጤና እንክብካቤ፣ መጠለያ፣ ደህንነት፣ ሥራ ወዘተ ያሉ የኑሮ ፍላጎቶችን ያካትታል።

ስትራቴጂካዊ የሥርዓተ-ፆታ ፍላጎቶች (strategic gender needs)፡- ከሥርዓተ-ፆታ አለመመጣጠን መንስኤዎች ጋር የሚዛመዱ የረጅም ጊዜ እና በግልፅ የማይታዩ ጉዳዮች/ፍላጎቶች ናቸው። እነዚህ ፍላጎቶች እንደየሀገሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ ላይ ይወሰናሉ። እነዚህ ስትራቴጂካዊ ፍላጎቶች ሲሟሉ በወንዶች እና በሴቶች መካከል በኃይል ግንኙነቶች ላይ ለውጦች እና መሻሻሎች ይኖራሉ።

ሴቶችን ማብቃት (women's empowerment)፡- ሴቶች በህይወታቸው ላይ የራሳቸውን ምርጫ እንዲወስኑና አላማቸውን እንዲያሳኩ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን እውቀት፣ አቅምና ሀብት እንዲያገኙ የማስቻል ሂደት ነው።

ማህበራዊ ማካተት (social inclusion)፡ ማህበራዊ ማካተት ማለት በተለያየ ምክንያት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ወይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች ወዘተ) በልማትም ሆነ በህብረተሰቡ ውስጥ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማስቻል ሂደት ሲሆን ይህም ሂደት በህግ፣ በፖሊሲ ወይም በሌሎች እርምጃዎች ሊተገበር ይገባል።

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጥ በጀት (gender responsive budgeting) ፡- ይህ በአንድ ሀገር የኢኮኖሚያዊ ግቦች እና በስርዓተ-ጾታ እኩልነት መካከል የበለጠ ወጥነት መኖሩን ለማረጋገጥ የሚተገበር የበጀት አወጣጥ ዘዴ ነው።

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት (gender based violence): በሴቶችና በወንዶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ዓይነት አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ድርጊት ሲሆን በሰላምም ሆነ በጦርነት ወቅት በግልም ሆነ በማህበራዊ (አደባባይ) ህይወት ያሉትን መሰረታዊ ነጻነቶች ላይ አግባብ ያልሆነ ገደቦችን መጣል ይጨምራል። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት እና ፆታዊ ጥቃት በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

አስገድዶ መድፈር (Rape): የተጎጂ ፈቃድ ሳይኖር በማስፈራራት፣ በማስገደድ፣ በማገት፣ የሥነ ልቦና ጫና በመፍጠር ወይም መከላከል ወይም ትክክለኛ ፈቃድ መስጠት የማይችልን ሰው በማስገደድ ወይም በማናቸውም መንገድ መከላከል እንዳትችል/እንዳይችል በማድረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ወይም ለመፈጸም መሞከር፣ የመራቢያ አካልን መንካት፣ በፊንጢጣ፣ በአፍ ወይም መሳሪያ ተጠቅሞ ግብረ ሥጋ መስል ድርጊት መፈጸምን ወይም ለመፈጸም መሞከርን የሚያጠቃልል ነው።

ወሲባዊ ትንኮሳ (sexual harassment) : ማንኛውም ሰው ከሌላው ሰው ፈቃድ ውጪ የወሲባዊ ጥያቄን እንደቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ የሚቀርብ ወሲባዊ ጥያቄ ወይም ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለው የቃል ወይም የአካል ንክኪ ሆኖ አስነዋሪ በሆነ መልኩ ወሲብ ቀስቃሽ አካላትን አጋልጦ ማሳየትን፣ የሌላውን ወሲባዊ ፍላጎት ሊያነሳሱ የሚችሉ ጽሁፎችና መጽሔቶችን ለሌሎች ማሳየትን፣ ወሲብ አዘል ሁኔታን የሚያነጸባርቁ ቀልዶች፣ ቧልቶች፣ አስተያየቶች፣ ጥያቄዎች ፣ ገጠመኞች እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከሌላው ሰው ፈቃድ ውጪ መፈጸምን፣ ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ፆታን ማጥላላት፣ ማናናቅ፥ በኤሌክትሮኒክስ ወሲባዊ አዘል ይዘት ያላቸውን ምስሎች፣ ፎቶግራፎች ያለፈቃድ ማሳየት ወይም ማስተላለፍን፣ ለወሲብ በሚያነሳሳ መልኩ የአካል እንቅስቃሴ ለሌላው ወገን ማሳየትን፣ የአንድ ሰው ጾታ ወይም ተክለ ሰውነት ወይም አለባበስ የተመለከቱና ወሲባዊ ተፈጥሮ ያላቸው አስተያየቶች፣ ነቀፌታዎች፣ ያልተፈለጉና አዋራጅ መገለጫዎች፣ ቁጣ ቀስቃሽ ቅጽል ስሞችን መጠቀምን፣ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ በመጠቀም፣ በድህረ ገጽ፣ ወይም በሌሎች መሰል መንገዶች የአንድን ሰው ምስል በመጠቀም እና በማስመሰል ወሲባዊ ሕይወት የሚያጋልጡና የሚያንቋሽሹ ተግባራትን መፈጸምን፣ አንድ ሰው ከፍቃዱ ውጪ መዳሰስ፣ መተሻሸት፣ መሳም ወይም ሆን ብሎ ሌላ ሰው ለወሲብ የሚገፋፋ የአካል ግንኙነት መፍጠርን፣ አንድን ሰው በማንኛውም ቦታ በመከታተል በነጻነት የመንቀሳቀስ መብትን መጋፋትን፣ የስነ ልቦና ጫና ማሳደርን፣ ለትምህርት ወጤት፣ ለስራ መቀጠር፣ ለደረጃ እድገት ወይም ሌላ ሕጋዊ ተግባር ለመፈጸም ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥን፣ ወሲባዊ ድርጊቶችን በማስገደድ ለመፈጸም በማሰብ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች መቀማትና መደበቅን ያጠቃልላል።

የቤት ውስጥ ጥቃት (domestic violence): በማንኛውም ግንኙነት ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ የበላይነት ለማሳየት ወይም ለመቆጣጠር በማሰብ፣ የማስፈራራት፣ የማሸበር፣ የመጉዳት፣ የማዋረድ፣ የመውቀስ፣ የማቁሰል ድርጊቶችን በመፈፀም አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ስሜታዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃት መፈፀም ነው። (ድርጊቱን ፈጻሚው ከተጎጂ ጋር ቤተሰባዊ ትስስር ያለው ሲሆን፣ የፍቅር ግንኙነት ያላቸው፣ የትዳር አጋር ፣ የቀደመ የፍቅር ግንኙነት ያላቸው፣ የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኛሞች ሊሆኑ ይችላሉ። አንድን ድርጊት የቤት ውስጥ ጥቃት ነው ለማለት በተጎጂና በድርጊቱ ፈጻሚ መካከል ካለው ግንኙነት ውጪ በአንድ ቤት መኖር አስፈላጊ አይደለም።)

አካላዊ ጥቃት (physical violence): አንድን የፍቅር አጋር ወይም ሌላ ግለሰብ በመምታት፣ በማቃጠል፣ በመጎተት፣ በመቆንጠጥ፣ በመጎንተል፣ በጥፊ በመምታት፣ ፀጉር በመጎተት፣ በስለት በመቁረጥ፣

በመደብደብ፣ በመግረፍ፥ በጥፊ በመምታት፣ ህክምና በመከልከል፣ መጠጥ ወይም/እና ዕፅ እንዲጠቀም በማስገደድ ወይም ሌል ሀይል ወይም መሳሪያ በመጠቀም መጉዳት ወይም ለመጉዳት መሞከር ነው።

የአሲድ ጥቃት (acid attack) ፡ አንድን ሰው ለመግደል፣ አካሉን ለማበላሸት፥ ለማጉደል ወይም ለማሰቃየት በማሰብ በሰውነት ላይ ወይም በሰውነት ውስጥ አሲድ ወይም ሌላ ጉዳት የሚያደርስ ንጥረ ነገር (ኬሚካል) በመርጨት የሚፈፀም ጥቃት ነው።

ኢኮኖሚያዊ ጥቃት (economic violence): አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የኢኮኖሚ ጥገኛ እንዲሆን በማሰብ ሀብቱን እንዳይጠቀም ወይም እንዳይቆጣጠር ወይም የጋራ የሆነን ሀብት መደበቅ፣ ማሸሽ ወይም መከልከል ወይም ቀለብ መከልከል ወይም ራሱን ችሎ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ መከልከል ወይም ለመከላከል መሞከርን የሚያጠቃልል ነው።

ስነ ልቦናዊ ጥቃት (psychological violence) : ተደጋጋሚ ትችት፣ ማዋረድ፣ አሉታዊ ቅጽል ስም መስጠት፣ ስም ማጥፋት፣ የቃላት ጥቃት፣ ሀሣብን ማቃለል፣ ማሸማቀቅ፣ ወይም ከልጆቻቸው ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያበላሽ ንግግር መሰንዘር ወይም ከጓደኛ እና ከቤተሰብ እንዲነጠል በማድረግ እና ሌሎች መሰል ድርጊቶችን በመፈጸም አንድ ሰው ስለራሱ ያለው ዋጋና ግምት እንዲቀንስ ማድረግ ነው።

ወሲባዊ ጥቃት (sexual violence): በጥቃት ፈፃሚውና በተጠቂው መካከል ያለው ግንኙነት ምንም ቢሆን በቤት ውስጥ፥ ወይም በትምህርት ቤት፣ በአገልግሎት መስጫ ቦታ ወይም የስራ ቦታ በአካልም ሆነ ኢንተርኔትና ሌሎች ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎችን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች ሀይል በመጠቀም የሚፈፀም የወሲብ ድርጊት፥ የወሲብ ድርጊት ሙከራ ወይም በፆታዊነት ላይ የተቃጣ ድርጊት ነው።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች (harmful practices): የሰውን አካላዊ፥ ወሲባዊ ወይም ስነልቦናዊ ደህንነት ወይም የሰብአዊ መብቶችንና የሰውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎ የሚጥሱ ስር የሰደዱ ልማዳዊ ድርጊቶችን ይጨምራል። ድርጊቱ የሴት ልጅ ግርዛትን፥ የልጅነት ጋብቻን፥ ጠለፋን፥ የሚስት መውረስን፥ በጋብቻ ላይ ጋብቻን፣ የትዳር አጋር መደብደብን ያጠቃልላል።

ሕገወጥ የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር (trafficking of women and children) : ሴቶችንና ሕጻናትን ለብዝበዛ ዓላማ ዛቻን፣ ሀይልን ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴን በመጠቀም፣ በማገት፣ በመጥለፍ፣ በተንከል፣ በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ የሰዎችን ለጥቃት ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ሃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመሰጠት ወይም

በመቀበል መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማዘዋወር፣ ማስጠለል ወይም መቀበል ነው። ወሲባዊ ብዝበዛ እና በግዳጅ ለዝሙት ተግበራ መጠቀም፣ የጉልበት ብዝበዛና፣ ባርያ ማድረግ ወይም ተመሳሳይ ተግባር መፈጸም ወይም በባርነት መያዝ ወይም የሰውነት አካልን መንቀል/መውሰድ የብዘበዛ ዓይነቶች ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው።

ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች (vulnerable groups): ባላቸው ገፅታ ወይም በሚገኙበት ሁኔታ ምክንያት ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃትና መድልዎ ይበልጥ ጉዳት የሚደርስባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያመለክት ሲሆን ሴቶችን፣ ህፃናትን፣ አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ በስደተኛ መጠለያ ካምፕ የሚገኙ ሰዎችንና የከባድ በሽታ ተጠቂዎችን ያጠቃልላል።